# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የስጦታ አሰጣጥ አፈጻጸም
## መመሪያ ቁጥር 478/2013

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 478/2013
# <u>የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የስጦታ አሰጣጥ አፈጻጸም መመሪያ</u>

በሀገራት መካከል የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት የሚያጠናክሩ ዓለም አቀፋዊ ኩነቶች ላይ ሀገሪቱን የሚወክሉ እና የሚያስተዋውቁ ባህላዊ ምርቶችና አገልግሎቶች በመለዋወጥ የባህል ዲፕሎማሲን ማሳደግ በማስፈለጉ፣

የሀገሪቱን ባህላዊ ቅርሶች እና ዕሴቶች በተለያዩ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ የግንኙነት መድረኮች በማስተዋወቅ፣ ሀገራዊ ገፅታን መገንባት በማስፈለጉ፣

ሚኒስቴሩ ከተለያዩ የዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የሀገራት ባለስልጣናት፣ ዲፕሎማቶች፣ ኢንቨስተሮች እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ጋር የሚያደርጋቸውን የአጋርነት ግንኙነቶች ለማጠናከር የስጦታ አሰጣጥ አሠራር ሥርዓትን መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በሀገራችን ህዝቦች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር የባህል ለባህል ልውውጦችን በማካሄድ ማህበራዊ ትስስርን ማጠናከር በማስፈለጉ፡፡

ከሀገሪቱ የፋይናንስ ሥርዓት ጋር የሚጣጣም ወጥ፣ ግልፅና ፍትሐዊ የስጦታ አሠጣጥ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ግንኙነት እንዲያደርግባቸው በህግ የተፈቀዱ ተግባራትን ለማከናን ይህንን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

   ይህ መመሪያ "የስጦታ አሰጣጥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 478/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **"ስጦታ"** ማለት የሀገሪቱን ወካይ የባህል ሀብቶችን ለማስተዋወቅ እና የዘርፉን ግንኙነቶችንና አጋርነትን ለማጠናከር የሚሰጥ የባህል ምርት ወይም አገልግሎት ነው፤
   2) **"የባህል ምርት"** ማለት የብሔር ብሔረሰቦችንና ህዝቦች የባህል አልባሳት፣ ባህላዊ መገልገያ ቁሳቁሶች፤ ወካይ ታሪካዊና ባህላዊ ስዕሎችንና መጽሐፍትን፣ በብርቅዬ

ዱር እንስሳት የተቀረጸ ምስል እና የቡና ምርትን እንዲሁም መሰል ወካይ የባህል ምርቶችን ያጠቃልላል፡፡

3) **"ባህላዊ አገልግሎቶች"** ማለት የባህል ምግብና መጠጥ፣ ተፈጥሮአዊና ባህላዊ ቅርሶች ጉብኝትን፣ ባህላዊ ክብረ በዓላትን፣ የባህል ስፖርትን፣ የባህላዊ ተግባራት ልምምዶሽ እና ሌሎች መሰል አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡
4) **"ዘርፍ"** ማለት የባህል፣ ቱሪዝም እና የስፖርት ዘርፍ ነው፡፡
5) **"ዲፕሎማት"** ማለት አንድን ሀገር በመወከል ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራ ሰው ነው፡፡
6) **"ክልል" ማለት** በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ መስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
7) **"የበላይ አመራር" ማለት** የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ዴኤታዎች፤
8) **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** እንደደቅደም ተከተላቸው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
9) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
10) በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

3. **ዓላማ**

በዘርፉ ከሀገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ አካላት ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች አጋርነትን እና ትብብርን ለማጎልበት የሚያስችል ግልፅ፣ ወጥና ፍትሐዊ የስጦታ አሰጣጥ ሥርዓትን መዘርጋት ነው፡፡

4. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ዘርፉን በሚመለከት በሚፈጠሩ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የስጦታ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት

5. **ስጦታ ስለሚሰጣቸው የሀገር ውስጥ አካላት**

ሚኒስቴሩ በዘርፉ ከተለያዩ አካላት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት አጋርነትና ትብብርን ለመደገፍ ለሚከተሉት የሀገር ውስጥ አካላት እንደአግባብነቱ ስጦታ ሊሰጥ ይችላል፡-

1) ዘርፉ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን እንዲያበረክት ለሚደግፉ አካላት፡-
   ሀ. ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣
   ለ. ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣
   ሐ. ለሀገሪቱ ፕሬዚዳንት፤

2) በህግ ስልጣን በተሰጣቸው መሠረት የዘርፉን ዕድገት በመደገፍ ተጨባጭ ሀገራዊ ፋይዳ ለሚያበረክቱ የፌዴራል ተቋማት የበላይ አመራር፤
3) የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን እንዲያጠናክሩ ለሚሰሩ የክልል ፕሬዚደንቶችና ከንቲባዎች፤
4) ለዘርፉ ሁለንተናዊ ልማት በሀብታቸው ለሚደግፉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፡፡

## 6. ስጦታ ስለሚሰጣቸው የዓለም አቀፍ አካላት

ሚኒስቴሩ፣ በዘርፉ ከተለያዩ የዓለም አቀፍ  አካላት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት አጋርነትና ትብብርን ለመደገፍ ለሚከተሉት አካላት እንደአግባብነቱ ስጦታ ሊሰጥ ይችላል፡-

1) የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር ከተለያዩ ሀገራት ተወክለው ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ልዑካኖች፤
2) በሀገር ውስጥ በሚካሄዱ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ኩነቶች ላይ ለሚሳተፉ ዲፕሎማቶች፣ የተቋማት መሪዎችና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች፤
3) በሚኒስቴሩ ግብዣ ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት ለዘርፉ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ሊያደርጉ ለሚችሉ ዲፕሎማቶች፣ የተቋማት መሪዎችና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች፤
4) በሀገር ውስጥ መቀመጫ ላላቸው የተለያዩ ሀገራት ዲፕሎማቶች፣ ተቋማት መሪዎች፤
5) የሚኒስቴሩ የበላይ አመራሮች በተለያዩ የሥራ አጋጣሚዎች ወደ ውጭ ሀገራት ሲንቀሳቀሱ ለሚያገኟቸው የመንግስት ኃላፊዎች፣ የተቋማት መሪዎችና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች፤
6) ለሀገሪቱ በዘርፉ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ዲፕሎማቶች፣ ተቋማት መሪዎች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች፤

## 7. ስጦታ ለመስጠት የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎች

ሚኒስቴሩ፣ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እና 6 ለተመላከቱ አካላት ስጦታዎችን ለመስጠት ከሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ መሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

1) ስጦታው በዘርፉ ከተለያዩ አካላት ጋር የሚደረጉ የአጋርነትና ትብብር ግንኙነቶችን የሚደግፍ መሆኑን፤
2) የሀገሪቱን ህዝቦች አብሮነት በማጠናከር ማህበራዊ ትስስርን የሚያበረታታ መሆኑን፤
3) ስጦታው የሚሰጠው አካል የዘርፉን ልማት ለመደገፍ የሚያስችል የሥራ ኃላፊነት ወይም አቅም ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤
4) ስጦታ የሚሰጠው አካል ከዚህ ቀደም ለዘርፉ ልማት ያበረከተው ተጨባጭ አስተዋፆ መኖሩ ሲረጋገጥ፣

5) ስጦታው የሚሰጠው አካል ሀገሪቱን በተለያዩ መድረኮች በማስተዋወቅ መልካም ገፅታ መገንባት የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

8. **<u>ስለ ስጦታዎች አግባብነት</u>**

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ ስጦታዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡-

1) ስጦታው የሀገሪቱን ብዝሀ ባህል በተገቢዉ ሁኔታ የሚወክል መሆኑ፤
2) ስጦታዉ የሀገሪቱን አቅም ያገናዘበ መሆኑን፤
3) በሀገሪቱ ህዝቦች መካከል ማኅበራዊ ትስስርን የሚያጎለብት መሆኑን፤
4) የሀገር ገጽታ የሚገነባ መሆኑን፤

9. **<u>የሚኒስቴሩ ኃላፊነት</u>**

1) የስጦታውን የግዥ ወጪ በበጀት ያስደግፋል፡፡
2) ለስጦታው የሚውሉ አገልግሎቶችና እቃዎች በመንግስት ግዥ መሠረት በውስን ጨረታ ወይም በዋጋ ማቅረቢያ ወይም ከአንድ አቅራቢ በሚፈፀም ግዥ ያከናወናል፡፡
3) የሀገሪቱን ብዝሀ ባህል የሚወክሉ ባህላዊ ምርቶች፣ የፈጠራ ሥራዎች ወይም ባህላዊ አገልግሎቶች በተገቢው ጥራት እንዲሰሩ ያበረታታል፤
4) በሚሰጡ ስጦታዎች ላይ ሀገሪቱንና ሚኒስቴሩን የሚወክል መለያ እንዲቀረጽባቸው ያደርጋል፤

10. **<u>የሚኒስትሩ ልዩ ስልጣን</u>**

1) ሚኒስትሩ፣ እንዳስፈላጊነቱ ለሀገራት መሪዎች፣ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀኃፊ እና በልዩ እንዲስተናገዱ ለሚወሰንላቸው አካላት ፈረስ እስከወግ እቃው በስጦታነት ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) ሚኒስትሩ፣ በልዩ ሁኔታ የሚስተናገዱ አካላትን እንዳግባብነቱ ይወስናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

12. **<u>ተጠያቂነት</u>**

በዚህ መመሪያ ከተደነገገው ውጪ ስጦታ እንዲሰጥ የፈቀደ ኃላፊ ወይም እንዲፈቀድ ያደረገ ባለሙያ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

13. <u>የማስፈፀም ኃላፊነት</u>

1) የሚኒስትር ፅህፈት ቤት የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፡፡
2) ለስጦታነት የሚውሉ ምርቶችና አገልግሎቶችን ደረጃና ጥራት በመለየት ግዢው እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡
3) በስጦታነት የሚሰጡ ምርቶችና አገልግሎቶች ከሚመለከታቸው አካላት በነፃ የሚገኝበትን መንገድ እንደአስፈላጊነቱ ሊያመቻች ይችላል፡፡

14. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎችና ልማዳዊ አሠራሮች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

15. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

16. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በሚኒስቴሩ ተፈርሞ በገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና በማግኘት በልዩ ፍቃድ እንዲስተናገድ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ----------------- ቀን 2011 ዓ.ም.**